# አውደ ኢትዮጵያ

ሐምሌ 20 2008 | የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ህጋዊ መንግሥትንና ፍትሃዊ ስርዓትን የመጠየቅ መብት አለው! | እትም 12

## ኦሎምፒክ-ኢትዮጵያ-አንድነት

ለመጀመሪያ ጊዜ በኦሎምፒክ ለኢትዮጵያ የወርቅ ሜዳሊያ ያስገኘው፣ አበበ ቢቂላ ሮም በተደረገው ማራቶን በባዶ እግሩ ሮጠ ነበር።

ሮም የኢትዮጵያ ደመኛ አገር የነበረችዋ የጣሊያን ዋና ከተማ ናት። በሮም፣ ቤኒቶ ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን









በወረረ ጊዜ፣ በአዲስ አበባ የጣሊያን ባንዲራ በመተከሉና ኢትዮጵያ በጣሊያን እጅ በመውደቋ የድንፋታ ንግግር ለአገሬው ሕዝብ ያደረገበት ከተማ ናት። ከሃያ ስድስት አመታት በኋላ፣ እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር በ 1952 ዓ.ም፣ ሙሱሊኒ በደነፋባትና የኢትዮጵያ ባንዲራ መሬት በመውደቁ ጨቤ በተረገጠባት ከተማ፤ የኢትዮጵያ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ ከፍ ብሎ ተውለበለበ። በዚያን ቀን ታሪክ ተሰራ። የኢትዮጵያን አለመኖር ይመኙ የነበሩ ጣሊያኖች ብቻ ሳይሆን በአለም ሁሉ ዘንድ ኢትዮጵያ ስሟ ተጠራ።

አበበ ቢቃላ አገሩን ለማስጠራት የተንቀሳቀሰው ልዩ ነገር ይዞ አልነበረም። የኢትዮጵያዊነት ኩራቱንና እግዚአብሄር የሰጠውን ጤነኛ እግሩን ይዞ እንጂ። በሚያውቀውና በሚመቸው መንገድ በባዶ እግሩ ለትውልድ የሚያኮራ ሥራን ሰራ።

አበበ ቢቂላ፣ ከአራት አመት በኋላ፣ ለሁለተኛ ጊዜ በቶክዮ ጃፓን፣ በብዙ ሺህ ሕዝብ ፊት የኢትይጵያ ባንዲራ እንዲውለበለብም አድርጓል። ሌላ አራት አመት ጨምሮ ለሶስተኛ ጊዜ በማራቶን ወርቅ ለማገኘት ያደረገው ሙከራ ግን በሕመም ምክንያት ተጨናገፈበት። ማራቶኑን ከጨመረ በኋላ ወደፊት መሄድ አልቻለም። ደከመ። አበበ ቢቃላ ቢደክምም ኢትዮጵያዊነት አልወደቀም።

በዚያን ጊዜ አብሮ ያለ ወንድሙ፣ ማሞ ወልዴ ተነሳ። የድልና የማዕረግ ችቦውን ከአበበ ቢቂላ ተቀበለ። ኢትዮጵያ በተከታታይ ለሶስተኛ ጊዜ የማራቶን አሸናፊ ለመሆን በቃች ። የኢትዮጵያ ባንዲራ ከባንዲራዎች በላይ በሜክሲኮ ዋና ስቴዲየም ከፍ ብሎ ተውለበለበ። ማሞ ወልዴ ከማራቶን ድሉ ባሻገር በአሥር ሺህም ተወዳድሮ የብር ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆኗል።

ከአራት አመት በኋላ ኦሎምፒኩ እንደገ በአወሮፓ ሙኒክ ጀርመን አገር ተደረገ። አንጋፋው ማሞ ወልዴ በማራቶን ነሐስ ይዞ እንደገና በኦሎምፒክ ሜዳ ኢትዮጵያን ሲያስጠራ አትሌት ምሩጽ ይፈጠርም ብቅ አለ። ለኢትዮጵያ በአሥር ሺ የብር ሜዳሊያ አስገኘ።

በደቡብ አፍሪካ ለነጻነት ትግል በሚደረገው እንቅስቃሴ ኢትዮጵያን ጨምሮ የአፍሪካ አገሮች፣ ምዕራባውያን ለአፓርታይድ አገዛዝ ይሰጡ የነበረውን እገዛ በመቃወም በካናዳ ሞትሪያል በ 1968 ከተደረገው የኦለምፒክ ውድድር እራሳቸውን አገለሉ።

የአጼ ኃይለስላሴ መንግስት በወታደራዊው መንግስት በተተካ በስድስት አመቱ ደግሞ የኦሎምፒክ ተራው የሶቭየት ሕብረት ሆነ። በዚያም ኢትዮጵያ አራት ሜዳሊያዎችን አገኘች። ምሩጽ ይፈጠርና ማሃመድ ከድር ተቀናቃኛቸውን በጋራ በማድከም፣ በመረዳዳትና በመነጋገር ለኢትዮጵያ ታሪክ ሰሩ። መሃመድ ከድር ተወዳድሪዎች ስላደከመለት የመጨረሻው ዙር ላይ ምሩጽ ይፍጥር አፈትልኮ ወጣ። አለምን አስደነቀ። ማርሽ ቀያሪው የሚል ቅፅልም ተሰጠው።

በቀዝቃዛው ጦርነት ምክንያት፣ ኢትዮጵያ የሶቭየት ሕብረት አጋር ስለነበረች ከሎስ አንጀለሱ የ 1976ና የ ሴኡል ኮሪያ 1980 ኦሎምፒክ እራሷን አገለለች።

ኢሕአዴግ አዲስ አበባን በተቆጣጠረ በአመቱ በ1984 በስፔን ባርሴሎና እህታችን ደራርቱ ቱሉ የኢትዮጵያን ባንዲራ እያውለበለበች የኢትዮጵያዊነት ኩራቷን ገለጠች። በአስር ሺህ በኦሎምፒኩ ብቸኛ የወርቅ ሜዳሊያ ለኢትዮጵያ አስገኘች። ኢትዮጵያዊያን ሁሉ፣ በአገር ቤትና በአለም ዙሪያ በደስታ ፈነጠዙ። የኢትዮጵያዊነት ኩራት ፈነጠቀ።

ደራርቱ ቱሉ ብቻ አልነበረችም፣ ፊጣ ባይሳ በ አምስት ሺህ አዲስ አበበ በአሥር ሺህ በባርሰሎና ኦሎምፒልክ ለኢትዮጵያ የነሐስ ሜዳሊያ አስገኝተዋል።

በ1986 ዓም የኦሎምፒኩ ውድድር ከአሥራ ሁለት አመት በኋላ ወደ አሜሪካ መጣ። ተራው የአትላንታ ጆርጂያ ሆነ። በዚህ ወቅት ነበር እነ ኃይሌ ገብረስላሴና ሮባ ፋቱማ ያሸበረቁበት። ሮባ ፋቱማ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ የሴቶች ማራቶን አሸናፊ እንድትሆን አደረገች። ሴቷ «አበበ ቢቂላ» ሆነች። ኃይሌ ገብረስላሴ በአሥር ሺህ ኢትዮጵያን ቀዳሚ ሲያስደርግ ዋቢ ጌጤ በአሥር ሺህ ለኢትዮጵያ ነሐስ አስገኘች። በአትላንታ ኦሎምፒክ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ርዕሰ አንቀጽ

# አንድነት ፓርቲ የፕሬስ ነፃነት እንዲከበር ይታገላል፤ እራሱም ያከብራል

መሻሻል ያለባቸው አንዳንድ አንቀጾችም ቢኖሩትም፣ የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት በአብዛኛው የዜግችን የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት የሚያረጋግግጥ ሰነድ ነው። ይህ ሰነድ በግልጽ ያስቀመጣቸው መሰረታዊ የዲሞክራሲያዊ መብቶች አሉ። ከነዚህም ውስጥ የመናገር፣ ሃሳብ በነጻነት የመግለጽና የፕሬስ ነጻነት ይገኙበታል።

የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት አንቀጽ 29ን ብንመለከት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ፣ ከመንግስት መረጃ የመጠየቅ፣ መረጃ የመቀበል እንዲሁም መረጃ የማስተላለፍ ሙሉ ህጋዊ መብት እንዳለው ያረጋግጣል። በዚሁ አንቀጽ የፕሬስ ነጻነት ሙሉ ለሙሉ የተረጋገጠ ሲሆን ሴንሰርሺፕ በምንም መልኩ አይፈቀድም።

ይህ ብቻ አይደለም፣ መንግስት ባጀት መድቦላቸው የሚንቀሳቀሱ የሕዝብ የመገናኛ ብዙሃንንም በተመለከተ አድሎ በሌለበት መልኩ የተለያዩ ሃሳቦችን ማስተናገድ እንዳለባቸው ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 29 ይደነግጋል።

ማንኛውም ሕገ ወይም መመሪያ፣ ሕገ መንግስቱን የሚጻረር ከሆነ ተግብራዊ እንደማይሆን አንቀጽ 9 ይናገራል። የፌዴራልም ሆነ የክልል አስተዳደሮችም ከሥራ ድርሻቸው መካከል ዋናውና ቀዳሚው ይህንን ሕገ መንግስት ማክበርና ማስከበር ነው።

ለምሳሌ አንቀጽ 52 የክልል አስተዳደሮች የአገሪቷን ሕገ መንግስት ማስጠበቅ እንዳለባቸው ያስቀምጣል። አንቀጽ 74 ፣ የአገሪቱ የፌደራል መንግስት ጠቅላይ ሚኒስትር ያላቸውን የሥራ ሃላፊነት ሲዘረዝር ንዑስ አንቀጽ 13 ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሕገ መንግስቱ መገዛትና ሕገ መግስቱን ማስከበር እንዳለባቸው በግልጽ ያስቀምጣል።

በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ የሚታየው እውነታ ግን ሕገ መንግስቱ፣ ሕገ መንግስቱን ማስከበር በነበረበት አካል ሲሸረሸር ነው። ሕገ መንግስቱ ፣ በአብዛኛው ዲሞክራቲክ አገራት እንደሚታየው የበላይ ሲሆን አይታይም። ይልቅ አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ገዢ ፓርቲ እራሱን ከሕገ መንግስቱ በላይ አድርጎ ሲንቀሳቀስና የሕዝብ የዲሞክራቲክ መብት ሲገሰስ ነው የምናየው።

ለምሳሌ በጥቅምት 1998 በርካታ ጋዜጠኖች አለአግባብ ታስረው ወደ ሁለት አመት ገደማ በእሥር ቆይተዋል። እንደነ ሰርካለም ፋሲልና እስክንድር ነጋ የመሳሰሉ አንጋፋ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች ሕገ መንግስታዊ መብታቸውን ተጠቅመው ጋዜጣ እንዳያወጡ የኢሕአደግ መንግስት ቃላቀባይ ጽ/ቤት የሆነው ማስታወቂይ ሚኒስቴር ሕገ ወጥ በሆነ መልኩ ከልክሏቸዋል። በቅርቡ የአዲስ ነገር ዋና አዘጋጅ አቶ መስፍን ነጋሽ፣ የቴዎድሮ ካሳሁን ጠበቃ የሆኑት አቶ ሚሊዮን፣ ዳኛ ልኡል ገብረማሪያምን እከሳለሁ ማለታቸውን በመዘገቡ ለእሥር ተዳርጓል። እዚህ ላይ ዜጎች በነጻነት ሃሳባቸውን የመግለጽ መብታቸው በግፍ ሲደፈር ነው የምናየው።

በክልሎች አከባቢ ያለው አፈና ደግሞ በአዲስ አበባ አሚታየው እጅግ የከፋ ነው። ይህም የሚያሳየው የክልል አስተዳደሮች ነጻ የመረጃ ልውውጥ እንዳይደረግ አፈና እያደረጉ መሆናቸው ነው።

አንቀጽ 29 በገዢው ፓርቲ መጣሱን በግልጽ ከሚያሳዩት ግልጽ መረጃዎች መካከል የኢትዮጵያን ቴሌቭዥንና ሬዲዮን መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ሁለቱ የመገናኛ ብዙሃን በሕዝብ ገንዘብ የሚንቀሳቀሱ አካላት ናቸው። ሕገ መንግስቱ የተለያዩ ሃሳቦችን ያለአድልዎ እንዲያቀርቡ ያዛቸዋል።

ነገር ግን በነዚህ ሁለቱ የመገናኛ ብዙሃን የምናየው ከሕገ መንግስቱ ውጪ የሆኑ አሰራሮችን ነው። ሃስቦች በነጻነት ሲንሸራሸሩ አይታይም። የተቃዋሚ መሪዎች በመንግስት አንዳንድ ፖሊሲዎች ላይ ያላቸውን ቅሬታ እንዲያሰሙ መድረክ አይሰጣቸውም።

ለምሳሌ የቅንጅት ህጋዊም የሞራልም ወራሽ የሆነውና በሕዝብ የሚወደደው አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ፣ እራሱን እንደገና አዋቅሮ ለመንቀሳቀስ ያደረገው አመርቂ ጥረት በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን አንድ ጊዜም ዘገባ አልቀረበበትም። በአዲስ አበባ የሚታተሙ የግል ጋዜጦች፣ የጀርመን ሬዲዮ፣ የአሜሪካን ድምጽ እንዲሁም በርካታ ድህረ ገጾች የአንድነትን ፓርቲ ዜና በሰፊው ሲዘግቡ፣ የመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ግን የአንድ ፓርቲ ፕሮፖጋንዳ መሳሪያ ብቻ ሆነው ነበር የቆዩት።

ሌላው ሊጠቀስ የሚችለው በቅርቡ በሚያሳዝን መልኩ በፓርላማ ጸድቆ የወጣው የፕሬስ ሕግ ነው። ይህ አዲስ የወጣው የፕሬስ ሕግ ፕሬሱን የሚጎዳና የፕሬስን ነጻነት ወደ ኋላ የሚጎትት ነው። በዚህም ምክንያት በርካታ የነጻው ፕሬስ አባላት ትልቅ ተቃውሞ አቅርበውበታል። ሬፖርተር ጋዜጣ « ከፕሬስ እጻነት ሽሽት» ሲል እንቢላታ «ወደ ኋላ የተጓዘው አዲሱ የፕሬስ ሕግ» ብሎ ይህንን በቅርብ የወጣውን የፕሬስ ሕግ ጎጂነት ዘግበዋል። የአውራምባ ታይምስ ዋና አዘጋጅ የሆኑት አቶ ዳዊት ከበደ « ሕገ መንግስቱን የሚጻረር የፕሬስ ሕግ» በማለት ይህ ሕግ ሕገ መንግስቱን ከማስከበርና የዜጎችን የመናገር፣ የመጻፍ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ከማስከበር ይልቅ የሚያፍን እንደሆነ ለእምቢልታ ጋዜጣ በሰጠው ቃለ መጠይቅ አብራርተዋል።

ለምሳሌ ሕገ መንስግቱ ማናቸውንም አይነት ሳንሱር በአንቀጽ 29 ይከለክላል። ይህ አዲስ የወጣው የፕሬስ ሕግ ከፕሬስ ጋር በተያያዘ ተፈጸመ ለሚባለው ወንጀል ከፍተኛ ቅጣት ስለሚጥል የጋዜጣ አዘጋጆች ከፍርሃት የተነሳ ሃሳባቸውን በጋዜጣቸው ላይ ከማስፈር እራሳቸውን በራሳቸው እንዲከለክሉ የሚያደርግ ነው። በሌላ አባባል ሰልፍ ሴንሰርሽፕ ይፈጥራል ማለት ነው። ይህ ሕገ መንግስቱን የሚጻረር ነው።

የፕሬስ ነጻነት ዲሞክራሲን ለመገንባት በሚደረገው ሂደት ቁልፍ ነው። የፕሬስ ነጻነት በሌለበት የዲሞክራሲ ሥርዓትን መገንባት አይቻልም። ህዝብ መረጃን ማግኘት ካልቻለና ከፕሮፖጋንዳ የፀዳ በእውነት ላይ የተመሰረተ መረጃ በሰፊው በማይሰራጭበት ሁኔታ የይስሙላ ምርጫ ብቻ በማድረግ ዲሞክራሲን መገንባት አይቻልም።

ቅንጃት ከሁለት አመታት በፊት «ፓርላማ እንገባ አንገባ» በሚለው ውይይት ወቅት ስምንት ቅደመ ሁኔታዎችን ማስቀመጡ ይታወሳል። ከነዚህ ቅድመ ሆኔታዎች አንዱ ሜድያው ነጻ እንዲሆን የሚጠይቅ ቅድመ ሆኔታ ነበር። በሌላ አባባል የሕገ መንስግቱ አንቀጽ 29 በሥራ ተግባራዊ ይሁን የሚል ነበር ከስምንቱ አንዱ የቅንጅት ቅድመ ሆኔታ።

አሁንም የቅንጅት ወራሽ የሆነው አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የሜዲያውን ነጻነት በተመለከተ የማያሻማና የማያለሳልስ ጠንካራ አቋም ነው ያለው። አንቀጽ 29 እንደሚለው የሜዲያው ነጻነት መረጋገጥ አለበት። የፌዴራል መንግስትም ሆነ የክክል አስተዳዳሪዎች ሕገ መንግስቱን መሸርሸር አቁመው ለሕገ መንግስቱ ተገዢ መሆን ይጠበቅባቸዋል። አንድነት ፓርቲ የፕሬስ ነፃነት ይኑር፤ ዜጎች የመፃፍና የመናገር መብት ይኑራቸው ሲል፤ በራሱ በፓርቲው ውስጥም ይህንን መብት በማስከበር ነው። በፓርቲው መተዳደርያ ደንብ አንቀፅ 41 ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው፤ የፓርቲው የፕሬስ ውጤቶቸ በብሄራዊ ምክር ቤቱ በሚመሰረት ቦርድ የሚመራ ሲሆን፤ ቦርዱም ተጠሪነተ ለዚህው አካል ነው። የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ በቦርዱ ሥራ ላይ ጣልቃ የመግባት ስልጣን የለውም። ይህም በደርግ ዘመን ከነበረው ‘ሠርቶ አደር’ ጋዜጣና አሁን ካሉት የህወሃትና ኢህአዴግ ፕሬስ ውጤቶች የተለየ ያደርገዋል። አንድነት ፓርቲ የፕሬስ ነፃነትን አስከብራለሁ ሲል፤ እራሱም ጭምር እያከበረው ለመሆኑ ማስረጃ ነው።

ከሕገ መንስግቱ ውጭ የሚያወጡትን ማናቸውም መመሪያም ሆነ «ሕግ» በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9 እንደተጠቀሰው ተቀባይነት አይኖረውም።

ስለዚህ አሁን የወጣው የፕሬስ ሕግ ሕገ መንግስቱን የሚጻረር ስለሆነና ተቀባይነት ሊኖረውም ስለማይችል የኢትዮጵያ የሕዝብ በአስቼካይ ተወያይቶ ሕገ መንግስቱን ባልጣሰ መልኩ ማሻሻያ እንዲያደርግበት ያስፈልጋል። እንደውም ፤ እንደ አንዳንድ ባለሙያዎች አስተያየት ከሆነ፤ በህገ-መንገስቱ ላይ የመፃፍና የመናገር፤ ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብቶች በትክክል የተቀመጡ ስለሆነ፤ ፕሬሱን በተመለከተ ሌላ ህግ አስፈላጊ አይደለም ብለው ይከራከራሉ።

ሕገ መንግስቱ እንደሚያዘው በሕዝብ ገንዘብ የሚተዳደሩ የመገናኛ ብዙሃን በባለሞያዎች እንዲጎለብቱና የአንድ ፓርቲ የፕሮፖጋንዳ መሳሪያ ከመሆን ይልቅ ሕዝብን ሞያዊ በሆነ ብቃት እንዲያገለግሉና በትክክል እውነትን እንዲዘገቡ የሚደረግበት ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲመቻች አንድነት ፓርቲ ትግሉን አጠናክሮ ይቀጥላል።

# ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያምና አቶ አሥራት ጣሴ በሰሜን አሜሪካ

በሀገሪቱ ወያኔን ያካተተ ብሔራዊ እርቅ እንዲመጣ ነው ብለዋል።

በተለያዩ ከተሞች በተካሄደው ህዝባዊ ውይይት ላይ ሰፊ ጊዜ ወስዶ ህዝቡን ያወያየው፤ አንድነት ፓርቲ የመረጠው ህጋዊና ሰላማዊ የትግል ስልት ነው። ከወያኔ ባህርይ በመነሳት፤ ሰላማዊው ትግል ተስፋ አስቆራጭ ነው፤ አያዋጣም፤ ከቅንጅት አንማርም ወይ፤ ግንባር ላይ ተኩሶ ከሚገድል ፓርቲ ጋር ሰላማዊ ትግል ማካሄድ አይቻልም የሚሉ አስተያየቶችና ጥያቄዎች በርከት ብለው ተነስተዋል። አቶ አስራትና ፕሮፌሰር መስፍን በዚህ ሀሳብ ዙርያ በሰጡት አስተያየት፤ የሰላማዊ ትግሉ ውጤት የሚለካው በወያኔ ድክመት/ጥንካሬ ሳይሆን በኢትዮጵያ ህዝብ ውሳኔና ቆራጥነት ነው ብለዋል። ህዝቡ ታግሎ የሚያታግል፤ በደንብ የተደራጀና ህዝብን



የማስተባበር አቅም ያለው፤ በዕቅድ የሚመራ ፓርቲ ካገኘ፤ የህዝብ ሀይል ምንጊዜም ቢሆን ለድል ይበቃል ብለዋል። አንድነት ፓርቲ ሰላማዊውን የትግል ስልት ሲመርጥ፤ ትግሉ ቀላል ይሆናል፤ መንገዱም አልጋ በአልጋ ነው በሚል ታሳቢ ሳይሆን፤ ህጋዊና ሰላማዊውን ትግል በመርህ ደረጃ በመቀበሉ ነው ብለዋል። የሰላማዊ ትግል ውጤት፤ ለሀገሪቱ ዘላቂ ሰላምን፤ ፍትህና ዲሞክራሲን፤ እንዲሁም ብልጽግናን ሲያረጋግጥ፤ ጦር ለሰበቀ ጦር የሚለው መርህ፤ ሀገሪቷን ከጦርነት አዙሪት አያላቅቅም።

አንድነት ፓርቲ የቅንጅት የሞራልም ህጋዊም ወራሽ ነው ያሉት አቶ አሥራት ጣሴ፤ ገዥው መንግስት በፈጠረው ሰንካላ ምክንያት ስሙን ለመቀየር መገደዱን፤ ይሁን እንጂ የትግል አለማውም ይሁን ዩትግል ስልቱን እንዳልቀየረ፤ አፅንኦት በመስጠት አስረድተዋል። ከቅንጅት ድክመቶች በመማር፤ በፓርቲው ውስጥ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚሰፍንበት፤ ስልጣን በተወሰኑ ሰዎች እጅ ተጠቃሎ እንዳይገባ፤ 'ቼክ ኤንድ ባላንስ' መፈጠሩን አስረድተዋል። የአንድነት ፓርቲ ምስረታ ወቅት ለሊቀመንበርነት ቦት ሶስት ሰዎች ከፍተኛ ፉክክር አድርገው ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ በአብላጫ ድምፅ ማሸነፋቸውንና፤ ደ/ር ሽመልስ ተ/ጻድቅ ደግሞ የብሄራዊ ምክር ቤቱ ሊቀመንበር መሆናቸውን እንደምሳሌ ጠቅሰዋል።

አንድነት ፓርቲ ቀዳሚ ተግባሩ፤ ዕውቅና በማግኘት ህጋዊ ሆኖ በሀገር ውስጥ መንቀሳቀስ ሲሆን፤ ይህም አንጋፋው ምሁር፤ የሰብአዊ መብት ተከራካሪና ፖለቲከኛ የሆኑት ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም እንዲሁም የአንድነት ፓርቲ ዋና ፀሃፊ አቶ አሥራት ጣሴ፣ በሰሜን አሜሪካ የተለያዩ ከተማዎች ያካሄዷቸው ህዝባዊ ስብሰባዎች በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቃቸውን ዘጋቢዎቻችን ገለፁ።

ስበሰባዎቹ እንዲዘጋጁ የረዳውና እንግዶቹን የጋበዘው የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት/አንድነት ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ማህበር መሆኑ ሲታወቅ፣ ስብሰባዎቹ የተካሄዱትም በዋሽንግተን ዲሲ፣ ቦስተን ማሳቹሰትስ፤ ሲያትል ዋሽንግተን፤ ዳላስ ቴክሳስ፤ ሚኒያፕልስ ሚኒሶታ፤ ላስ ቬጋስ ኔቫዳ፤ ሳን ሆሴ ካሊፎርኒያ፤ ሎስ አንጀለስ ካሊፎርኒያ እና አትላንታ ጆርጂያ ናቸው። ስብሰባዎቹ ጁላይ …. በዋሽንግተን ዲሲ ተጀምሮ ኦገስት 10 2008 በአትላንታ ጆርጅያ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቀዋል። የእንግዶቹ ጉብኝትና ስብሰባዎች፤ አንድነት ፓርቲ የመሰራች ስብሰባውን ካካሄደ በኋላ የመጀመርያው መሆኑ ነው።

ዘጋቢዎቻችን ከየከተማው እንደዘገቡት ከሆነ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በየከተማው ስብሰባው ላይ የተካፈሉ ሲሆን፤ በወቅቱ የሀገራችንና የአንድነት ፓርቲ ጉዳዮች ላይ እጅግ ጠቃሚ የሆኑና ሰፋ ያሉ ውይይቶች ተካሂደዋል።

ውይይት ከተካሄደባቸው ነጥቦች ውስጥ ፥

1. በሥልጣን ላይ ያለው መንግስት 'ጠላት' ነው ወይስ አይደለም?
2. አንድነት ፓርቲ በመርህ ደረጃ የተቀበለው ሰላማዊና ህጋዊ የትግል ስልት
3. አንድነት ፓርቲ ከቅንጅት በምን ይለያል፤ ምንስ ልምድ ቀስሟል?
4. አንድነት ፓርቲ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምን ሰንቋል?
5. በውጭ ከሚገኘው ደጋፊ፤ ፓርቲው ምን ይጠብቃል?
6. በቅርብ የተመሰረተው 'መድረክ' ውስጥ የአንድነት ፓርቲ ሚና ምድንነው?
7. ከኢትዮጵያ ተቆርሶ ለሱዳን ስለተሰጠው መሬት ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ጥያቄዎች ናቸው።

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም፤ በዋሽንገተን ዲሲ ባደረጉት ንግግር፤ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ወያኔ/ኢህአዴግ ፍፁም አምባገነን፤ በጣም ጨካኝ፤ እጅግ የተሳሳቱ ፖሊሲዎችን የሚያራምድ፤ በዛም ምክንያት ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ ሰብአዊ መብቶች የሚጣሱባት፣ ዲሞክራሲ ያልሰፈነባትና፣ በፖለቲካዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሂደቶች ወደኋላ እየተንደረደረች ያለች መሆኗን ጠቅሰው፤ ይሁን እንጂ ወያኔ ተቀናቃኝ እንጂ ጠላት ሊባል አይገባም ብለዋል። ጠላት ማለት ሊያጠፋት የሚፈልጉት ሲሆን፤ የአንድነት ፓርቲ ፍላጎት ወያኔን ማጥፈት ሳይሆን በቅርቡ ይፈፀማል ሲሉ አቶ አስራት እምነታቸውን ጠቅሰዋል። ፓርቲው 11 ቋሚ ኮሚቴዎች እንዳሉት የገለፁት አቶ አሥራት፤ ቀጣይ ተግባሩ፤ ህዝብ የማስተባበርና የማደራጀት ሥራ የሚሰራ ሲሆን፤ ለዚህም ተግባር በሀገር ውስጥ በሚገኙ ዞኖችና ወረዳዎች ፅ/ቤት ለማቋቋም ታቅዷል። ለዚህም ተግባር ወደ 912 000 የአሜሪካን ዶላር በአመት ያስፈልጋል ብለዋል።

ህዝብ ለለውጥ ዝግጁ መሆን አለበት ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፤ በአሁኑ ወቅት በሀገር ጉዳዮች ላይ ማንም ተመልካች መሆን አይገባውም ብለዋል። አቶ አሥራት በበኩላቸው፤ በተለይ በውጭ ሀገር የሚገኘው ደጋፊ፤ በጉልበት በዕውቀትና በገንዘብ ድገጋቸውን መቀጠል አለባቸው ብለዋል።

ወያኔ በቅርቡ ለሱዳን መንግስት ቆርሶ የሰጠውን



መሬት በተመለከተ በተለይ ለፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። ፕሮፌሰር መስፍን የመልክዓ-ምድር ምሁር ከመሆናቸውም በላይ፤ በቀደሙት መንግስታት ውስጥ የኢትዮ-ሱድን ድንበርን አስመለክቶ ጥናት ያካሄዱ ምሁር ናቸው። በቅርቡ የተከሰተውን የድንበር ሁኔታ አስመልክተው፤ ከመንገስት አካላት እውነታውን ለማግኘት አስቸጋሪ ስለሆነ ኢትዮጵያውያን ገንዘብ በዋጣት የሰው ሀይል ወደ አከባቢው ልከው፤ መረጃ ማሰባሰብ አለባቸው ብለዋል። በመረጃ ላይ የተመሰረተ ትንታኔ መስጠት የሚቻለው የዛኔ መሆኑን ጠቅሰው፤ ወያኔ ዝም ከተባለ ሀገራችን ተሸንሽና ልታልቅ ትችላለች ብለዋል።

በየከተማዎቹ ከተካሄዱት ትላልቅ ህዝባዊ ውይይቶች በተጨማሪም፤ በርካታ የእራት ምሽቶችና ለየት ያሉ ፕሮግራሞችም ተካሂደዋል። በዚህም ወቅት በየአከባቢው ካሉ ምሁራን ባለሃብቶችና በኢትዮጵያ የዲሞክራሲና ፍትህ ትግል ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያበረከቱ ግለሰቦች ጋር ጠቃሚ የሆነ ውይይቶች ተደርገዋል። በተለይም በሳን ሆሴ ፤ ካሊፎርኒያ እንግዶቹ ከተለያዩ ታዋቂ ዩኒቨርስቲ የተወጣጡ ኢትዮጵያ ውያን ወጣቶች ጋር ለመወያየት ችለዋል። በቦስተን ማሳቹሰትስ ደግሞ፤ እንግዶቹ የከተማው ቁልፍ ተበርክቶላቸዋል።

ሁለቱ እንግዶች፤ በሰሜን አሜሪካ ያደረጉትን ህዝባዊ ውይይቶች አጠናቀው በቅርቡ ወደ ሀገር ቤት እንደሚመለሱ ለማወቅ ተችላል።

# ኦሎምፒክ-ኢትዮጵያ...

ከገጽ 1 የዞረ

ኢትዮጵያ ሶስት ሜዳልያ ስታገኝ ሁለቱ የተገኙት በሴቶች እህቶቻችን ነበር።

ኢትዮጵያ እስከ አሁን ብዙ ሜዳሊያ ያገኘችበት ኦሎምፒክ በ1990 የተደረገዉ የሲድኒ ኦሎምፒክ ነበር። ያኔ ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ ሚሊዮን ወልዴና አበራ ገዛኸኝ አልተቻሉም። የወንዶች አሥር ሺህ፣ የሴቶች አሥር ሺህ፣ የወንዶች አምስት ሺህና የወንዶች ማራቶን በኢትዮጵያ አሸናፊነት ተጠናቀቀ። ማሞ ወልዴ በሜክሲኮ ማራቶንን ካሸነፈ ጊዜ ጀምሮ ተወስዶብን የነበረዉን ቦታ አበራ ገዛኸኝ በሲድኒ አስመለሰ።

በዚሁ የሲድኒ ውድድር ጌጤ ዋሚ በአሥር ሺህ ብርን፣ በአምስት ሺህ ነሐስ ስታስገኝ፣ መዝገበ አሰፋ በአሥር ሺህ ፣ ተስፋዬ ሞላ ደግሞ በማራቶን ነሐስ ለኢትዮጵያ አስገኝተዋል።

በአቴንስ ኦሎምፒክ ቀነኒሳ ፣ ስለሺ እንዲሁም አንጋፍዉ ኃይሌ ገብረስላሴ እነ ምሩጽ ይፍጠር በሞስኮ እንዳደረጉት ሁሉ ኢትዮጵያዉያን ከተረዳዱ፣ ከተያያዙ፣ ከተነጋጋሩና አብረዉ ከሰሩ መቋቋም የሚያቅታቸዉ መሰናክል እንደሌለ በዉጤታቸዉ ለዓለም አሳዩ። «ሽልሞን ሸኝቶን አገር፤ አሲዞን ሰንድቀ ዓላማ፣ መርደ ነዉ ለወገናችን ማሸነፍ ካቃተንማ" እያሉ መርደን ሳይሆን ለኢትዮጵያ ህዝብ ኩራትን አለበሱት።

ቀነኒሳ በአሥር ሺህ ፣ መሰረት ደፋር በአምስት ሺህ ወርቅ ተሸላሚ ሲሆኑ፣ ስለሺ ስህኔና እጅጋየሁ ዲባባ ብርን ደራርቱ ቱሉና ጥሩነሽ ዲባባ ነሐስን አስገኝተዋል።

አበበ ቢቂላ፣ ማሞ ወልዴ፣ ምሩጽ ይፍጠር፣ መሀመድ ከድር፣ እሸቱ ቶላ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ አዲስ አበበ፣ ፊጣ ባይሳ፣ ሮባ ፋጡማ ፣ ኃይሌ ገብረስላሴ፣ ጌጤ ዋሚ፣ ሚሊዮን ወልዴ፣ አበራ ገዛኸኝ፣ መዝገቡ አሰፋ፣ ተስፋዬ ቶላ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ መሰረት ደፋር፣ ስለሺ ስህኔ.፣ እጅጋየሁ ዲባባ፣ ጥሩነሽ ዲባባ፣ በአጠቃላይ፣ ሃያ አትሌቶች ፣ ለኢትዮጵያ ክብር ሲሉ ወዛቸዉን፣ ጉልበታቸዉ አቅማቸዉን ሰጥተዉ፣ 14 የወርቅ፣ 5 የብርና 12 የነሐስ ሜዳሊያዎችን ለኢትዮጵያ በማስገኘት፣ ቢያንስ ቢያንስ ለትንሽ ጊዜ ከጦርነት፣ ከረሃብ፣ ከሰብዓዊ መብት ረገጣ ..ከመሳሰሉ አሳዛኝ ወሬዎችና ድርጎቶች በተቃራኒ ዓለም የኢትዮጵያን ውበት፤ ጀግንነትና ኩራት እንዲያዩ አድርገዋል።

ኢትዮጵያዉያን በተከፋፈሉበትና እርስ በርስ በሚባሉበት በአሁኑ አሳዛኝ ወቅት ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በአንድ ላይ ለማምጣት እነዚህ የኦሎምፒክ አትሌቶቻችን ችለዋል። የገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች፣ የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎች፣ በዉጭ አገር የሚኖሩ፣ በአገር ቤት በአዲስ አበበ፣ በናዝሬት በወለጋ፣ በጎንደር በአፋር በሃረር በአክሱም እንዲሁም በተለያዩ ከተሞችና በገጠር ያሉ ኢትዮጵያዉያን ሁሉ ትኩረታቸዉ በቤጂንግ የኢትዮጵያን ስም ለማስጠራት የተሰለፉ ወገኖቻችን ላይ ነዉ። በዚህ ወቅት ሁላችንም ምኞታችን አንድ ነዉ።

አበበ ቢቂላ በባዶ እግሩ ማራቶንን ካሸነፈ፣ በባዶ እግሩ ታሪክ ከሰራ እኛም አሁን ታሪክ መስራት እንችላለን። ደራርቱ ቱሉ ኩራቷ የሆነዉ የኢትዮጵያ ባንዲራ ይዛ በአለም ፊት እንዳዉለበለበች እኛም ኢትዮጵያን ማስጠራት እንችላለን።

እርግጥ ነዉ አሁን ድሃ ነን። በእግራችን ላይ «ጫም» የለም። እርግጥ ነዉ ገና ብዙ ይቀረናል። እርግጥ ነዉ በፊታችን ያለዉ ፈተና ከባድ ነዉ። እርግጥ ነዉ ብዙ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር አለ። እርግጥ ነዉ ጨለማዉ ጠንክሯል። ነገር ግን በባዶ እግራችን ኢትዮጵያን ከሩጫ ባለፈ መልኩ በዓለም የተከበረች ማድረግ እንችላለን። የሚያስፈልገዉ ቁርጠኝነትና ከራስ ጥቅም ይልቅ ለአገር ማሰብ ነዉ። የሚያስፈልገዉ «ይቻላል!» የሚል ዉሳኔ ነዉ። የሚያስፈልገዉ ቀበቶንና መቀነትን መታጠቅና ጠበቅ ማድረግ ነዉ።

አበበ ቢቂላ በሜክሲኮ በደከመዉ ጊዜ ማሞ ወልዴ ተካዉ። ኃይለ ገብረስላሴ እግሩን በታመመ ጊዜ ስለሺና ቀነኒሳ ቀደሙ። እንዲህ አይነቱ የመረዳዳት፣ የመተያየት፣ አንዱ ሲወድቅ ሌላዉን የማንሳት መንፈስ ነዉ የሚያስፈልገን። «እኔ አልቻልኩም። አገር ከምትሰደብ የኔ ወርቅ ይቅር። አንተ ቅደም» የሚሉ ይመስላሉ አበበ ቢቂላ ለማሞ ወልዴ፣ ኃይሌ ገብረስላሴ ደግሞ ለ ስለሺና ለቀነኒሳ ። ይህ ራስ ወዳድነት ላይና «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» የሚል አስተሳሰብ ላይ ያተኮረ ሳይሆን አገር በመዉደድ ላይ ያተኮረ ኩሩ ሥራ ነዉ።

ከአትሌቶቻችን የምንማረዉ ሌላዉ ትልቁ ቁም ነገር በግል የትም እንደማንደርስ ነዉ። ክብርን ከፈለግን በጋራ መስራት አለብን። ኢትዮጵያ በአለም እንድትታወቅና ከሃፍረቷ እንድትወጣ ካስፈለገ መንገዱ አንድና አንድ ብቻ ነዉ። እርሱም የኢትዮጵያዊያን በጋርና በአንድነት መቆም። ጉልበታችንንና ገንዘባችንን ሌላዉን ኢትዮጵያዊ ወገናችንን በማጥቃትና በማዋረድ ላይ ማጥፋቱን ማቆም አለብን። እልህና ቂም በቀል ባህል፣ በፍቅርንና በይቅርታ፣ በመተሳሰብና በወንድማማችነት መተካት አለበት። የደከመዉን የደኸየውንና የወደቀዉን ወገናችን ማንሳት እንጂ በወገናችን ላይ እየተረማመድን እኛ እንዲያልፍልን መሞከር የለብንም።

ታዋቂዉ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ጆን ዔፍ ኬኔዲ ለሕዝባቸዉ የተናገሩት አንድ ትልቅ አባባል ነበር። «አገሬ ለኔ ምን ታደርግልኛለች ብለን ሳይሆን እኔ ለአገሬ ምን እያደረኩኝ ነው ብለን መጠየቅ ነው ያለበን» ነበር ያሉት እኚህ ዝነኛዉ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት።

አትሌቶቻችን ለአገራቸዉ ክብር በቤጂንግ ይገኛሉ። እግዚአብሄር ብርታቱን ይስጣቸዉ። ለሚያደርጉትም መስዋእትነት እግዚአብሄር ያክብርልን። መልካም ዉጤት እንዲያገኙ እጅጉን ምኞታችን ነው። እግዚአብሄር ይርዳቸው ፤ ይከተላቸው።
እነርሱ ለአገራቸዉ እንደተሰለፉ፣ እኛ ደግሞ የነርሱን ድል ከመመኘትና ከመናፈቅ ጎን ለጎን እራሳችንን ጥያቄ መጠይቅ ይኖርብናል። ለአገራችን ኢትዮጵያ እኛስ ምንድን ነዉ የምናደርገዉ ? መቼ ነዉ በሩጫ ሳይሆን ባለንና በምንችለዉ ሁሉ የ«የወርቅ ሜዳሊያዎችን» ለኢትዮጵያ የምናመጣዉ ? መቼ ነዉ ኢትዮጵያን አንድ እርምጃ ወደፊት የምናራምደዉ ?

ኢትዮጵያዉያን በአራት አመት አንዴ ብቻ አይደለም በአንድ ላይ መምጣት የደስታ ባዕል ማድረግ ያለባቸዉ። አሁን፣ ነገ. ሁልጊዜ በአንድ ላይ መሆን አለብን። አንድነት ኃይል ነዉ።መከፋፈል የሕልዉና ፀር ነዉ።

አንዲት ግንድ ለብቻዋ ብዙም አትቀጣጠልም። ወዲያዉ ትጠፋለች። ከሌሎች ግንዶችና ቅጠሎች ጋር ከሆነች ግን ለሰዓታት እየነደደች ብርሃን ትሆናለች። አሁን በኢትዮጵያ ጨለማ ነዉ። አሁን ጦርነት ነዉ። አሁን ረሃብ ነዉ። አሁን መከፋፈል ነዉ። አሁን አምባገነንነት ነዉ። «እኔ ብቻ አዉቃለሁ የሚለዉ ፖለቲካ» አልሰራም።

ነገር ግን ከአትሌቶቻችን መማር አለበን። ለእርቅና ለሰላም ተዘጋጅቶ፣ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ላይ እራሱን በቅንነት እንዲያሳትፍና ከዚህ በፊት የተፈጠሩ ችግሮች በማይደገሙበት መልኩ አንድ እርምጃ ወደፊት በጋራ የምንሄድበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅበታል።

እንደ መንግስት ኢሕአዴግ ሃላፊነት አለበት። ኢትዮጵያዉያን በጋራ በጠረጴዛ ዙሪያና በንግግር ችግራቸዉን እንዲፈቱ ማድረግ ኢሕአዴግ ካልቻለ አገራችን ወደማይታሰብና ወደማይገመት ሁኔታ ላይ ልትወድቅ እንደምትችል የታወቀ ነዉ። ስለዚህም ኢሕአዴግ አትሌቶቻችን በኦሎምፒክ የሚያስገኙትን የአንድነት፣ አብሮ በጋራ የመሆንና የኢትዮጵያዊነትን ጨራ እንዳያጠፋዉ በጣም ያስፈልጋል። ይህ የአሁኑ ኢትዮጵያዊ ትዉልድ፣ ከሩጫ በተጨማሪ የሚኮራበትንና የሚጠራበትን ታሪክ መሥራት ይጠበቅበታል።

አትላነታ * ቦስተን * ችካጎ * ዳላስ * ዴነቨር * ሎሳንጀለስ* ላስሸገስ * ሚኒያፖልስ * ናሽቪል * ኦክላነድ
* ኦሃዮ * ፊኒክስ * ሳንሆዜ * ሲያትልን * ደቡብ ዳኮታ * አፓ ስቴኢት ኒዮርክ * ዋሽንግትን ሜትሮ

የቅንጅት ለአንድነት ለዲሞክራሲ በሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች መህበር
766 Rock Creek Church Rd., NW .Washington DC, 20010 *ስልክ (202) 541-0556
ፋክስ: (202) 541-0557.*ኢሜል: kinijitna@kinijitna.org
Www.kinijitna@kinijitna.org

አስተያየቶን በ awdeethiopia@gmail.com ይጻፉልን